## አጀንዳ ቁጥር 3
## <u>የገዥውን ፓርቲ ጥንካሬዎችና ድክመቶች መገምገም</u>

በዚህ አጀንዳ ላይ በተደረገው ግምገማ በቅድሚያ እስካሁን ድረስ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የተቃዋሚዎች ደጋፊ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ስለገዥው ፓርቲ ጥንካሬና ድክመት የነበራቸው ግንዛቤ ምን ይመስል እንደነበር ለመገምገም ተሞክሯል፡፡ በተደረገው ግምገማም በአብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ደጋፊዎቻቸው ዘንድ ገዥው ፓርቲ በማንኛውም ዓይነት መመዘኛ በጣም ደካማ ድርጅት ተደርጐ እንደሚታይ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የመንግሥት ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት የሕዝብ ድጋፍ የሌለውና ለጥቂት ዓመታት እንኳ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚያበቃው ድርጅታዊ ጥንካሬ እንደሌለው ተደርጐ ሲታይ የነበረ ቢሆንም ከዚህ ዓይነቱ የተቃዋሚዎች ግምገማ በተፃራሪ ገዥው ፓርቲ ለ17 ዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆየት መቻሉ፣ በአንፃሩም ከገዥው ፓርቲ የተሻለ ጥንካሬና የሕዝብ ድጋፍ አለን ብለው የሚያምኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለ17 ዓመታት ገዥውን ፓርቲ ታግለው ለማሸነፍ ካለመቻላቸውም በላይ በሂደት እራሳቸው እየተዳከሙ መምጣታቸው ሲታይ - ከመጀመሪያው ስለገዥው ፓርቲ ጥንካሬና ድክመት የነበራቸው ግምገማ ስህተት እንደነበረና ይህ ዓይነቱ የተሳሳተ ግምገማም በራሱ የተቃዋሚውን ጐራ ትግል በማዳከም ረገድ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው ግምገማው አስታውሷል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በወደፊቱ የትግል ጉዟቸውም የሚቀናቀኑትንና በሕዝብ ምርጫ ከሥልጣን ሊያወርዱት የሚፈልጉትን ገዥ ፓርቲ ጥንካሬና ድክመት በአግባቡ መገምገምና ለትግሉ የሚመጥን ትክክለኛ ስትራቴጂ መንደፍ የማይችሉ ከሆነ ምርጫ 97ን ተከትሎ የፈፀሙትን ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ስህተት ወደፊትም ሊደግሙት እንደሚችሉ ያለውን ስጋት ገልፆ የውይይት መድረኩ የገዥውን ፓርቲ ጥንካሬና ድክመት እንደሚከተለው ለመገምገም ሞክሯል፡፡

ግምገማው ገዥው ፓርቲ ከአጠቃላይ ድርጅታዊ ሁኔታና ከአገራዊ አጀንዳዎች አንፃር ያለውን ጠንካራና ደካማ ጐን ለማየት የሞከረ ሲሆን ከድርጅታዊ ሁኔታ አኳያ የድርጅቱን መዋቅራዊ ጥንካሬ፣ ህዝብን የማደራጀት አቅም፣ የአመራር ብቃትን፣ የፓርቲ አባላት የአላማ ፅናትና የስራ ትጋትን፣ ውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲንና ዲስፕሊንን እንደዋና መመዘኛዎች ወስዷል፡፡ ከአገራዊ አጀንዳዎች ጋር በተያያዘ ደግሞ ድርጅቱ በፕሮግራሙ ያስፈራቸውን የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አጀንዳዎችንና ድርጅቱ ከምስረታው እስከ አሁን ድረስም በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ያራመዳቸውን አቋሞች እንደዋነኛ መመዘኛዎች ወስዷል፡፡ በዚህም መሠረት ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ-

1. ከድርጅታዊ መዋቅር አንፃር እስካሁን አገሪቱ ውስጥ ከታዩ ሌሎች ፓርቲዎች በበለጠ (ከኢሠፓም በበለጠ) መዋቅሩን እስከ ቀበሌ ድረስ የተዘረጋ ግዙፍ ድርጅት መመስረት የቻለ መሆኑ፤
2. በውስጡ ከሌሎች ድርጅቶች የበለጠ የውይይትና የእርስ በርስ ግምገማ ባህል ያለው መሆኑ፤

3. አመራር አባላቱ እስካሁን በሌሎች ፓርቲዎች ባልታየ ሁኔታ ጠንካራ የእርስ በርስ መተማመንና ውስጣዊ ልዩነትን አቻችሎ የመቀጠል ብቃት ያላቸው መሆኑ፤

4. በ17 ዓመቱ የትግል ወቅት ያሰባሰባቸው ነባር አባላቱ በአብዛኛው ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውንና ንብረታቸውን ብቻ ሳይሆን አካላቸውንና ውድ ህይወታቸውን ጭምር ለአላማቸው መስዋዕት ለማድረግ የተዘጋጁ መሆኑ፤

5. አብዛኛው አባላቱ በትግሉ ሂደት በሚያጋጥማቸው አስቸጋሪ ሁኔታ በቀላሉ ተስፋ የማይቆርጡ፣ ከሽንፈታቸው ወይንም ከድክመታቸው እንደገና አንሰራርቶ ለመጠናከር ብርታቱ ያላቸውና ሕዝብን በድርጅታቸው ዙሪያ ለማሰባሰብ ሌት ከቀን የመስራት ትጋት ያላቸው መሆኑ፣

6. አብዛኛው አባላቱ በመካከላቸው ጠንካራ ጓዳዊ ስሜት የሚታይባቸውና በድርጅታቸውና በድርጅት መሪዎቻቸው ላይ ጠንካራ እምነት ያላቸው መሆኑ ከድርጅት ሁኔታ አንፃር የገኘው ፓርቲ ጠንካራ ጐኖች መሆናቸው በግምገማው ታምኖበታል፡፡

ከእነዚህ የድርጅት ውስጣዊ ሁኔታቸው በተለየ-

1. ድርጅቱ ከሕዝብ ጋር ባለው ግንኙነት ግልፅነትና ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሌለው መሆኑ፤

2. ድርጅቱ በሚያከናውናቸው አጠቃላይ ተግባራት የአገርን፣ የድርጅትንና የግለሰብን ጉዳዮች በአግባቡ ለይቶ የማየት አቅሙ ውስን መሆኑ፤

3. የድርጅት አባል ያልሆነን ሰው ሁሉ እንደ ስህተተኛና ኋላቀር አስተሳሰብ ያለው ሰው አድርጐ ማየትና ከዚያም በጠነከረ ሁኔታ በሃሣብ ተቃዋሚ የሆነን ሰው ሁሉ በጥርጣሬና በጠላትን ማየትና በአንፃሩ የድርጅቱ አባል የሆነን ሰው ሁሉ እንደ ሃቀኛ፣ ታማኝና አገር ወዳድ አድርጐ የማየት ባህሉ፤

4. በተለይም ድርጅቱ የመንግሥትነት ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ ያሰባሰባቸው አብዛኛዎቹ አባላት በድርጅቱ ዓላማ እምነት ኑሮአቸው ሳይሆን በድርጅቱ ዙሪያ ሊገኝ የሚችልን የግል ጥቅም ለመቀራመት የተሰባሰቡ መሆናቸውን መገንዘብ አለመቻሉ፣

5. በአጠቃላይም ድርጅቱ ከፕሮፓጋንዳ በፀዳ ሁኔታ በሕዝቡ ውስጥ የለውን የድጋፍና የተቃውሞ መጠን በአግባቡ መገንዘብ አለመቻሉና ያለፈ ስህተትን ለሕዝብ በይፋ የማመንና ሕዝብን ይቅርታ የመጠየቅ ባህል የሌለው መሆኑ ከድርጅት አንፃር የገኘው ፓርቲ ደካማ ጐኖች መሆናቸው ታምኖበታል፡፡

በአጠቃላይ ገዥውን ፓርቲ ከድርጅት አንፃር ለመገምገም በተደረገው ሙከራ ከላይ በድክመት ከተጠቀሱት ነጥቦች ይልቅ በጥንካሬ የተጠቀሱት ነጥቦች ከአንድ ድርጅት የጥንካሬ መመዘኛዎች አንፃር ሚዛን የሚደፉ ይዘት ያላቸው ሆኖ በመገኘቱ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከሌሎቹ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጋር ሲነፃፀር ገዥው ፓርቲ “ጠንካራ ድርጅት ነው” ሊባል እንደሚችል ታምኖበታል፡፡

ከአገራዊ አጀንዳዎች አንፃር የገዥውን ፓርቲ ጥንካሬና ድክመት ለመገምገም በተደረገው ሙከራ - ገዥው ፓርቲ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የሚያራምዳቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አጀንዳዎች የአፈፃፀም ሂደታቸውም ሆነ የመጨረሻ ውጤታቸው ከገዥው ፓርቲ የስልጣን የበላይነት መቀጠል ጋር የግድ ተጣጥመው እንዲገኙ ስለሚፈለግ- በዚህ ምክንያት ብዙውን ጊዜ አገርና ሕዝብ ጠቀም የመሆን እድላቸው የጠበበ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ አንድ ፓርቲ የሥልጣን የበላይነቱን ለረዥም ጊዜ አስጠብቆ ለመቀጠል የሚያራምዳቸው አቋሞች መልካም አስተዳደርንና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማምጣት ከሚችሉ ፖሊሲዎች ጋር ተፈጥሯዊ ተቃርኖ ስለአላቸው ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የሚያራምዳቸው አጀንዳዎች በአብዛኛው የአገርንና የሕዝብን ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር ደካሞች እንደሆኑ ታምኖበታል፡፡

በአንድ በኩል ገዥው ፓርቲ የፖለቲካ የበላይነትን ለማስጠበቅ የኢኮኖሚ የበላይነትን ማግኘት አለብኝ የሚል ፅኑ እምነት ስለሚያራምድ - የሚተገብራቸው ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ከነፃ ገበያ የኢኮኖሚ አስተሣሰብ ጋር የሚጣጣሙና ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በተገቢው መጠን ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ አልሆነም፡፡ የአገሪቱ የመሬት ፖሊሲና የፖለቲካ ድርጅቶች በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸው የእጅ አዙር ተሣትፎና ቁጥጥር ከዚህ “ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ኢኮኖሚውን መቆጣጠር” ከሚል ዘላቂ ሆኖ ሊቀጥል ከማይችል መሠረታዊ የአስተሳሰብ ህፀፅ የሚመነጭ መሆኑንም ግምገማው አስምሮበታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በገዥው ፓርቲ በኢህአዴግ ውስጥ ከትግሉ ምስረታ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ቁልፍ የፖለቲካ ሚና የሚጫወተው ድርጅት ህውኃት በመሆኑና ይህ ድርጅት ከሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም ሆነ አገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች አንፃር ጠበብ ያለ ማህበራዊ መሠረት (constituency) ያለው መሆኑ በአገራዊ የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ መስክ የራሱን ችግር እንዳስከተለ ግምገማው አምኖበታል፡፡ ህውኃት በኢህአዴግ ውስጥም ሆነ በአጠቃላይ በአገሪቱ የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ እራሱን ወሳኝና የበላይ አድርጎ ለማቆየት በሚያደርገው ጥረት ከአንድነት ይልቅ ለልዩነት፣ ከግለሰብ ይልቅ ለቡድን መብት ቅድሚያ እንዲሰጥና በአገሪቱ የሚገኙ ቁልፍ መንግሥታዊና ድርጅታዊ ተቋማትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቁጥጥሩ ስር ለማዋል የሚያስችለውን ስልት እንዲከተል አስገድዶታል፡፡ ይህ ዓይነቱ ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የራስን የሥልጣን የበላይነት ያስቀደመ ስልትም ገዥውን ፓርቲና ሕዝብን የሚያቃቃሩ ቅራኔዎችን የበለጠ እያጉለበተ ከመምጣትና ለመልካም አስተዳደር ፀር የሆኑ አስተሳሰቦችንና አሰራሮችን ከማጠናከር አንፃር የሚጫወተው አሉታዊ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ገዥው ፓርቲ ለፖለቲካ የኃይል ሚዛን የበላይነት (power politics) የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ ምክኒያት በአገራችን በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት የዴሞክራሲ፣ የነፃ ምርጫ፣ የነፃ ፕሬስና የሕዝባዊ ተቋማት ግንባታ ሂደቶች እየተጠናከሩ እንዳልሆነ ታምኖበታል፡፡ ኢህአዴግ የመገናኛ ብዙሐንን በበላይነት በመቆጣጠር ከሕዝብ ስሜትና ፍላጐት ጋር የማይጣጣም አሰልች ፕሮፓጋንዳ እየሰራ ለመቀጠል የተገደደው፣ የመንግሥትና የሲቪል ተቋማትን በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር በራሱ ቁጥጥር ስር አድርጐ ለመቀጠል

የፈለገው፣ ከነፃ ገበያ ሥርዓት በሚፃረር ሁኔታ የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በበላይነት ለመቆጣጠር ሲጥር የሚታየውና በአገሪቱ እንዲመጣ የሚፈለገው የልማት እድገትም ከራሱ ድርጅታዊ ፍላጐትና አቅጣጫ ጋር የተቃኘ እንዲሆን የሚፈልገው ከዚሁ ለፖለቲካ የሥልጣን የበላይነት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጠው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰቡ የመነጨ እንደሆነና ይህም በራሱ ገዥውን ፓርቲ በሕዝብ ዘንድ ልባዊ ተቀባይነት /Legitimacy/ እንዳሳጣውና ከአገራዊ አጀንዳዎች አንፃርም ደካማ አቋም ያለው ድርጅት እንዲሆን እንዳዳረገው ግምገማው አምኖበታል፡፡

በአጠቃላይም ገዥው ፓርቲ ከድርጅታዊ መዋቅርና አሠራር አንፃር ጠንካራ ሊባል የሚገባው ድርጅት ሲሆን ከአገራዊ አጀንዳዎች አንፃር ግን ከፍተኛ ድክመት የሚታይበት ድርጅት መሆኑን ግምገማው አምኖበታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ገዥውን ፓርቲ ከአገራዊ አጀንዳዎች አንፃር ደካማ ያደረጉት አስተሳሰቦች ብዙዎች እንደሚገምቱት ከገዥው ፓርቲ የእውቀት ማነስና አገርን ሆን ብሎ ለመጉዳት ከማሰብ የሚመነጩ ሳይሆኑ ከከፍተኛ የህልውና ስጋት አንፃር ለፖለቲካ የበላይነት /power politics/ ከመጠን ያለፈ ትኩረት በመስጠት የተከሰቱ ድክመቶች መሆናቸው ታምኖበታል፡፡ ገዥው ፓርቲ ከመጀመሪያው የትግል ምስረታው ጀምሮ እስካሁን ድረስ - የትግል ስልትን፣ የብሔር ጥያቄን፣ የኤርትራ ጥያቄንና የመሬት ጥያቄን በተመለከተ የወሰዳቸውና ያራመዳቸው አቋሞች በትግሉ ሂደት ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች በተሻለ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣትና የሥልጣን የበላይነቱንም ቀጣይ ከማድረግ አንፃር በጥንቃቄ  እየመረጠ ያራመዳቸው ከየወቅቱ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ /pragmatic/ አቋሞች እንደሆኑና ይህም ድርጅቱ በየጊዜው የሚወስዳቸውን አቋሞች ከራሱ ጥቅም አንፃር ምን ያህል በጥንቃቄ እንደሚያይና ውስጣዊ፣ አካባቢያዊና አለም አቀፋዊ የኃይል አሰላለፍንም ጭምር በፍጥነት የመገንዘብና እራሱን ከሁኔታዎች ጋር የመለዋወጥ ባህሪና አቅም ያለው ድርጅት መሆኑን እንደሚያሳይ ግምገማው አምኖበታል፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ገዥው ፓርቲ ከድርጅታዊ ጥቅሙ ጋር ይሄዳሉ ብሎ የሚያምንባቸውን ማናቸውም ዓይነት አቋሞችና አስተሳሰቦች ያለ ይሉኝታ በድፍረት ወደ ሕዝብ ይዞ በመቅረብ ከሕዝብና ከተቀናቀኝ ኃይሎች ሊመጡ የሚችሉ ተቃውሞዎችን የመጋፈጥ ብቃት ያለው ድርጅት መሆኑን፣ የዚህ ዓይነት ደፋር አቋሞቹም በአንድ በኩል እስካሁን ድረስ በሥልጣን ላይ እንዲቆይ አወንታዊ አስተዋፅኦ ያበረከቱለት ሲሆን - በሌላ በኩል ደግሞ በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ልባዊ ተቀባይነት /Legitimacy/እንዳያገኝና በአገሪቱም የተረጋጋ ሠላማዊ የፖለቲካ ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግ ረገድ የተጫወተው አሉታዊ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ግምገማው አስምሮበታል፡፡ ወደፊትም ገዥው ፓርቲ ድርጅታዊ ጥንካሬውን አገርና ሕዝብ ጠቀም ከሆኑ አጀንዳዎች ጋር ማጣጣም የሚችልበት ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ በድርጅታዊ ጥንካሬ ብቻ የተገኘ የሥልጣን የበላይነት ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ላይ የራስንም ሆነ የአገርን ህልውና ለሚፈታተን አደጋ እንደሚያጋልጥ ስጋቱን በመግለፅ ግምገማው ተጠናቋል፡፡